# ወያኔም ይወርዳል

(ከማህሉ በቀለ - ቶሮንቶ)

አገር የሚያጠፉ፣ በሽታ ገባና
ሀይማኖት ባህሉ፣ ኋላ ቀር ሆነና
ከበርቴው አርበኛው፣ ጠላት ተባለና
ይህ ትውልድ፣ በዛኛው ታጥቆ ተነሳና
በዕውር ርዕዮት፣ ህዝቡ ተመራና
ግራ እጅ ቀኙን እጅ፣ ቀንጥሶ ጣለና
እነሆ ሆነናል፣ አንጎለ ሰንካላ፡፡

ለኢትዮጵያ በማይሆን፣ በራሽያ መዶሻ
በጠማማው ማጭድ፣ በቻይና ማረሻ
በማይገጥም ጫማ፣ ስቃይ በሚያበዛ
እግር ሲቆማመጥ፣ እጅ ሲወረዛ
ያላየነው የለም፣ ያልቀመስነው ነገር
ተከድኖ ይብሰል ነው፣ እንዲያው የኛ ነገር፡፡

አንዱ ቤት፣ ለሁለት እየተከፈለ
ትውልድ በወላጁ፣ ቅጣት አስከተለ፡፡

ወንድየው ኢህአፓ፣ እህቱ መኢሶን
አባቱ ኢዲዩ፣ አማቹ ደርግ ሲሆን
ቤተሰብ ሲዋከብ፣ ቀበሌው ሲከለል
ማዘን ማሰብ ቀርቶ፣ ኑሮ ሲሆን በቀል
በጣም ተሳስተናል፣ እንዲያውም አብደናል
ስንገል ስንሞት፣ ብዙ አጥፍተናል፡፡

ንጉሡን ገልብጠን፣ ዜጎችን ረሽነን
እኛም በተራችን፣ ተገርፈን ተጠብሰን
ገራፊ ገዳይም፣ ነብሴ አውጭኝ ብሎ
ሲጠፋ ሲሰደድ፣ ሲሄድ አገር ጥሎ
ተገራፊም ደግሞ፣ ቂም አልረሳም ብሎ
በቀል በእርቀ ሰላም፣ አልተካም ብሎ
እንዲያው የኛን ጉዳይ፣ ዞር ብዬ ሳየው
በአበው አባባል፣ አፈር ማጠብ ነው፡፡

መጨረስ ባቃተን፣ በረጅሙ ሩጫ
እየተንጠባጠብን፣ ስንሆን ማላገጫ
ምንድነው የነካን፣ ምንድነው የሆነው
ዕርግማን አለብን፣ ወይንስ ተወግዘን ነው?

አገር ተበጣጥሶ፣ ክብራችን ተዋርዶ
ሥርዓት ተበርግዶ፣ መብታችን ተጎምዶ
በሾኬ ተመተን፣ በመለስ ኮማንዶ

ለአገር መጮሁ፣ ተስፋ አመንምኖ
ለክልል መቆሙ፣ ሹመት አምጭ ሆኖ
ነገር ሲጨማለቅ፣ ችግር መላ ሲያጣ
በጣም አስከፊ ነው፣ በኢትዮጵያ የመጣ፡፡

ምን አይነት ቅጣት ነው፣ በኛ የደረሰ
ምን አይነት ፍጡር ነው፣ ባገር የነገሠ
ግድግዳ የሚበሳ፣ ጣርያ እያፈረሰ
መሠረት የሚንድ፣ ወለል እያረሰ፡፡

ወያኔ የሚባል፣ የነመለስ መንጋ
ወይም አይታረቅ፣ ወይም አይዋጋ
በዲሞክረሲ ስም፣ ነጮቹን አታሎ
አበሻን አፍኖ፣ ደብድቦና ገሎ
ዘላለም የሚገዛ፣ የሚኖር መስሎት
አንደ አሞሌ ጨው፣ ስልጣኑ ጥሞት
ባገር ላይ በትኖ፣ እልቂትና ሞት
አልጋ ላይ ተቀምጧል፣ ወንበሩ ጠቦት፡፡

በኢትዮጵያ ትግል ውስጥ፣ የተፋለማችሁ
ወገን የጎዳችሁ፣ ወይ ያስቀየማችሁ
በንጉሥ ግልበጣው፣ የተሳተፋችሁ
በመንግሥቱም ጊዜ፣ ቦታ የያዛችሁ
በወያኔም ቢሆን፣ ሥፍራ ያገኛችሁ
ጥሩም ይሁን መጥፎ፣ ሥራ የሠራችሁ
አውቃችሁ ገብቷችሁ፣ ወይንም ተሳስታችሁ
ለኢትዮጵያ ጥፋት፣ ምክንያት የሆናችሁ
መናከስ መናቆር፣ ፍፁም ይቅርባችሁ
ወይንም ከዚህ ሁሉ፣ ቁጭ በሉ አርፋችሁ
ለችግር መፍትሔ፣ ማግኘት ካቃታችሁ
የበቀል አዙሪት፣ አስሮ ከያዛችሁ፡፡

እንዳለ የሚቆይ፣ አንድም ነገር የለም
ወያኔም ይወርዳል፣ ወደዛኛው ዓለም
ልክ እንደቀድሞቹ፣ እንደሱ ጠላቶች
እሱም ጠላት ሆኖ፣ ይጠፋል በሌሎች፡፡

ጨዋታው አንድ ነው፣ ሜዳውም ይኸው ነው
ዳኛ ግን መቀየር፣ ጥሩ መፍትሔ ነው
በጥሩ ቲፎዞ፣ በግሩም ጨዋታ
ማሸነፍ አለብን፣ የማታ የማታ
ድሉ የሕዝብ ሆኖ፣ ዋንጫውን ካስመለስን

ያንድነትን ጥቅም፤ ያኔ እናውቃለን♦